አንበሳ ባንክ
anbesa bank
እንጓምረው • LET'S GO FOR IT

የባለአክሲዮኖች 22ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ

የተከበራችሁ የአንበሳ ባንክ አ.ማ ባለአክሲዮኖች፡-

በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 1360/2017 አንቀፅ 14 (2 እና 3)፣ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(2)፣ 367፣ 370፣ 371፣372 እና በተሻሻለው የባንኩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 11 (7) መሰረት የአንበሳ ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 22ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቅዳሜ ነሐሴ 02 ቀን 2018 ዓ.ም. ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ አድዋ ሙዚየም ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በአካል ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓትና ቦታ እንድትገኙ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

- የባንኩ የተፈረመ ካፒታል፡- 5,915,611,000.00
- የባንኩ የተከፈለ ካፒታል፡- 5,915,611,000.00
- የባንኩ የምዝገባ ቁጥር፡- MT/AA/3/0055690/2015
- የባንኩ አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ
- ድህረ-ገፅ አድራሻ፡- www.anbesabank.com

የ22ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፡-

ድምጽ ቆጣሪዎች ተመርጠው ምልአተ ጉባኤው መሟላቱ ከተረጋገጠ በኃላ፡

1. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማጽደቅ፣
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማና አስመራጭ ኮሚቴ መምረጥ፤
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ማከናወን፣
4. የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ፣

ማሳሰቢያ፡-

- ባለአክሲዮኖች ወይም ወኪሎቻቸው በጉባዔው ለመገኘት ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደስ መታወቂያ፣ መንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ዋናውን ከፎቶ ኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡
- በጉባኤው በግንባር መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተዋካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም የወካዩን ባለአክሲዮን ኢትዮጵያዊነት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን ከኮፒ ጋር በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሰረት ጉባኤው ከመካሄዱ 3 ቀን በፊት 22 ማዞሪያ ሌክሰስ ኘላዛ ሕንፃ ውስጥ በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የሕግ አገልግሎት መምሪያ በአካል በመቅረብ ለዚሁ አላማ በማሕበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልቶ በመፈረም ተወካይ መሾም እና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ መሆንና ድምፅ መስጠት የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- የሚወከሉ ባለአክስዮኖች የሚቀበሉት የውክልና መጠን የራሳቸውን አክሲዮን ጨምሮ ከባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ከአስር (10) በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ